## በትምሕርት ቤት የረድኤት አጋዥ (ማህበራዊ ሰታሕተኛ) ምንድን ነው፣ ማንንስ ነው የሚመለከተው?

በትምሕርት ቤት የረድኤት አጋዥ (ማህበራዊ ሰታሕተኛ) ለተማሪዎች፣ ወላጆች፣ መምህራን እና ትምህርት ቤት እገዛን ይሰጣል::

**ተማሪት እንዲሁም ተማሪ** ቀልጣፋና ያልተወሳሰብ እገዛን ያገኛሉ:: በማህበረሰባዊ ኑሮ ዙሪያ ያሉ ጥያቄዎችን፣ ጭንቀት ወይም ጥል፣ በጋራ ወይም በግል ከትምሕርት ቤቱ የረድኤት አጋዥ (ማህበራዊ ሰታሕተኛ) ዘንድ የምክር እግዛ ልትወስዱ ትችላላችሁ:: እዛም ሁኔታውን በትክክል እንመለከታልን አብረንም መፍትሄን እንፈልጋለን::

**ወላጆች** ስለልጆቻችሁ አስተዳደግ ወይም በትምህርት ቤት አካባቢ ያሉ ሁኔታ ምትጨንቁ ከሆነ የትምሕርት ቤት የረድኤት አጋዦችን (ማህበራዊ ሰታሕተኞችን) ለትገናኟቸው ትችላላችሁ::

የትምሕርት ቤት የረድኤት አጋዥ (ማህበራዊ ሰታሕተኛ) እገዛን ይሰጣል፣ ነገሮችን ያብራራል፣ በቤትምህርት ቤት እና አስተዳደግ ዙሪያ ላሉ ጥያቄዎች እውቀት አለው እንዲሁም ጽህፈት ቤቱን (አሰራሩን) ያውቃል::

**መምህራን** በተለያዩ ከባድ ሁኔታዎች በግል እና በጋራ በትምሕርት ቤቱ የረድኤት አጋዥ (ማህበራዊ ሰታሕተኛ) ሊነጋገሩ ይችላሉ:: የሆኑ ችግሮች ብጋራ ይያዛሉ እንዲሁም ይታያሉ::

በትምሕርት ቤት የረድኤት አጋዥ (ማህበራዊ ሰታሕተኛ) በመላው **ትምህርት ቤት** ወይም / እንዲሁም በነጠካ **ክፍሎች** ተግባሮችን እና ፕሮጀክቶችን ያቀርባሉ እንዲሁም አብረው ያራምዳሉ::

## የትምሕርት ቤት የረድኤት አጋዥ (ማህበራዊ ሰታሕተኛ) እንዴት ይሰራል?

የትምሕርት ቤት የረድኤት አጋዥ (ማህበራዊ ሰታሕተኛ) በትምህርት ቤት ይገኛሉ፣ ቋሚ ጽሕፈት ቤትም አላቸው እንዲሁም በስልክ ሊገኙ ይችላሉ::

በግል የሚሰጡ የምክር አገልግሎቶች በምሰረቱ በፈቃደኝነት ነው:: የመጀመሪያ የምክር እገዛ ሃሳቡ በመምህራን ሊቀርብ ይችላል::

ይህ እገዛ **ሚስጥራዊ (ብሚስጥር የሚያዝ)** ነው:: የትምሕርት ቤት የረድኤት አጋዥ (ማህበራዊ ሰታሕተኛ) ሚስጥርን የመጠበቅ ግዴታ አለበት::

እገዛው በነጻ ነው::

## ወላጆች መቼ ንው በትምሕርት ቤት የረድኤት አጋዥ (ማህበራዊ ሰታሕተኛ) እገዛን ሊፈልጉ (ሊጠይቁ) ይችላሉ?

ስለ ልጆቻችሁ እድገት ምትጨንቁ ከሆነ ወይም አንድ የሚያስጨንቃችሁ ሁኔታ ካል::

በትምህርት ቤት ስላለ ሁኔታ ጥያቄ ካላችሁ::

ሳትጠይቁ ከሚቀር አንድ ጊዜ አብዝታችሁ ብትጠይቁ ይሻላል!

**ሁልጊዜ የትምሕርት ቤት የረድኤት አጋዥ (ማህበራዊ ሰታሕተኛ) እገዛ በሚያስፈልግበት ጊዜ፣ ችግር (ቀውስ) አለ ማለት አይደለም::**